የአዲሱ ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ

ረቂቅ ሠነድ

DRAFT

ይህ ሠነድ ለውይይት የተዘጋጀ እና እስከ ወረዳ ወርዶ ውይይት የሚደረግበት ሲሆን በፓርቲው ጠቅላላ ጉባዔ የሚፀድቅ ነው።

ማውጫ

ምዕራፍ I ፤ ጠቅላላ ድንጋጌዎች 3

አንቀፅ 1. አጭር ርዕስ 3

አንቀፅ 2. የፓርቲ ስያሜ አርማ፤ ሰንደቅ ዓላማ እና ዓላማው 3

ምዕራፍ II፡ የፓርቲው ድርጅታዊ መዋቅር 3

አንቀፅ 3. የፓርቲው አካላት 3

አንቀፅ 4. የፓርቲው ጠቅላላ ጉባዔ 6

አንቀፅ 5. የብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ 7

አንቀፅ 6፡ የብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ አባላት ሥልጣንና ተግባር/የጉባዔ ተመራጮች 9

አንቀፅ 7፡ የምርጫ ወረዳ/ክልል ..... **Error! Bookmark not defined.**

አንቀፅ 8፡ የሕዝብ ተመራጮች/ ፓርላማ ቡድን 11

አንቀፅ 9፡ ኦዲተር 12

አንቀፅ 10፡ የደንብ ተርጓሚና ዲሲፕሊን ኮሚቴ 12

አንቀፅ 11፤ የፓርቲው ዓለም አቀፍ ቻፕተር ..... **Error! Bookmark not defined.**

ምዕራፍ IV፡ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች 13

አንቀፅ 12. ኤዲቶሪያል ቦርድ 13

አንቀፅ 13. የፓርቲው ፅ/ቤት 13

አንቀፅ 14፡ አባልነት 13

14.1. ዕጩ አባል 14

14.2. ሙሉ አባል 14

14.3. ተባባሪ አባል/ደጋፊ 14

አንቀፅ 15. የአባልነት መብትና ግዴታ 15

DRAFT

አንቀፅ 16. አባልነት የሚቋረጥበት ሁኔታዎች 15
አንቀፅ 17. ፋይናንስ እና ንብረት 16
አንቀፅ 18. የፓርቲ ደንብ፣ ፕሮግራምና ፖሊሲዎች አጸዳደቅና አተገባበር 16
አንቀፅ 19፡ የጠቅላላ ጉባኤ የስነስርአት ደንቦች 17
19.1. የጉባኤ ደንቦች - 1 የጉባዔ አጠራር 17
19.2. የጉባኤ ደንብ - 2፡ የሪፖርትና አጀንዳ አቀራረፅ ..... **Error! Bookmark not defined.**
19.3. የጉባኤ ደንብ 3 - የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት ..... **Error! Bookmark not defined.**
አንቀፅ 20. የፓርቲው ብሄራዊ የስራ አስፈፃሚ ሃላፊዎችና የብሄራዊ ኮሚቴዎች አባላት ምርጫ 18
20.1. ጠቅላላ መርህ 18
20.2. የፓርቲ ሃላፊዎች አመራረጥ ሰነስርአት 18
አንቀፅ 22፡ ሰለ ደንብ መሻሻል 19
አንቀፅ 23፡ ሰለ ፓርቲው መፍረስ 19
አንቀፅ 24፡ የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች 19
አንቀፅ 25፡ ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ 20

DRAFT

ምዕራፍ *I* ፡ ጠቅላላ ድንጋጌዎች

አንቀፅ 1. አጭር ርዕስ

ይህ መተዳደሪያ ደንብ « የ ---------- ፓርቲ» (አአአአ) መተዳደሪያ ደንብ" ተብሎ ሊጠራ ይችላል።

የ -------- ፓርቲ በፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ ቁጥር .....በአገር አቀፍ ፓርቲነት የተመዘገበ ፓርቲ ነው።

አንቀፅ 2. የፓርቲ ስያሜ አርማ፤ ሰንደቅ ዓላማ እና ዓላማ

2.1. የፓርቲው ስያሜ አርማ እና ሰንደቅ ዓለማ

2.1.1. የፓርቲው መጠሪያ ስም አአአአxአአአ፣አአአአአአ አአአአአአ ሲሆን በአጭሩ (አአአአ) ተብሎ ሊጠራ ይችላል።

2.1.2. የፓርቲው ዓርማ ------ መደብ ላይ ---------- የያዘ ሆኖ በውስጡ ---------- ይኖረዋል። ትርጉሙም ----------፣ ---------- የኢትዮጵያዊ ዜጎችን ህብራዊነት እንዲሁም ---------እውቀትና በውይይት የሚያምን የፖለቲካ ማህበረሰብን ታሳቢ ያደረገ ነው።

2.1.3. የፓርቲው ዓርማ የፓርቲው፣ ሰንደቅ ዓላማ ሆኖ ያገለግላል። ትርጉሙ ከላይ በተራ ቁጥር 2. 1. 2 የተጠቀሰው ነው።

2.2. ዓላማና ተግባር

2.2.1. የአሳታፊ ዴሞክራሲ መርህን በመከተል በሁሉም የሃገሪቱ የምርጫ ክልል/ወረዳዎች ወስጥ ዜግነትን መሰረት ያደረገ የፓርቲው አባላት በባለቤትነት የሚቆጣጠሩት ድርጅታዊ መዋቅር መዘርጋት፣

2.2.2. አላማውንና እሴቶቹን የሚጋሩ አባላቱንና ደጋፊዎቹን በማስተባበር በጋራ እንቅስቃሴ በሃገራችን ለዴሞክራሲ ባህል መበልጸግና ለጠንካራ ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ መፍጠር በትጋት መስራት፣

2.2.3. የ.....ፓርቲ በየትኛውም እርከን በሚከናወኑ ዴሞክራሲያዊ የምርጫ ሂደቶች የ ፓርቲ ተወካዮች እንዲመረጡ መጣር፣

2.2.4. በመላው ሃገሪቱና በሃገሪቱ በሚገኙ የትኛዎቹም ምክር ቤቶች የ ..... ፓርቲን አሳታፊ ዴሞክራሲያዊ መርህን ተከትሎ ማደራጀትና ማንቀሳቀስ፣

2.3. የፓርቲውን ፕሮግራምና እና መተዳደሪያ ደንብ እንዲሁም በየወቅቱ በሚደረጉ የአባላቱ ጠቅላላ ጉባኤ የሚተላለፉ ውሳኔዎችን ተግባራዊ ያደርጋል።

ምዕራፍ II፡ የፓርቲው ድርጅታዊ መዋቅር፣

ፓርቲው ከታች ወደ ላይ በአሰታፊ ዴሞክራሲ መርህ የተመሰረተ ድርጅታዊ መዋቅር ይኖረዋል። የፓርቲ መዋቅር ከምርጫ ክልል/ወረዳ የሚጀምር ሆኖ በምርጫ ክልል/ወረዳ ተወካዮች የሚዋቀር ከፍተኛ የሥልጣን አካል የሆነ ጠቅላላ ጉባኤ ይኖረዋል። የፓርቲው አካላት የሚከተሉት ይሆናሉ።

አንቀፅ 3. የፓርቲው አካላት፣

3.1. የፓርቲው ጠቅላላ ጉባዔ፣ የፓርቲው አጠቃላይ ውሣኔ ሰጪ የሆነ በሦስት አመቱ ከወረዳ አባላት በውክልና በሚመጡ አባላት እንዲሁም በዚሁ ደንብ በሚዘረዘሩት ተሳተፊዎች የሚመሰረት ጠቅላላ ጉባኤ የፓርቲው መዋቀርና ከፍተኛው የስልጣን እርከን ነው።

DRAFT

3.2. የፓርቲ ኮንፈረንስ፣ ከየወረዳ የምትወከል (የሚወከል) አንድ ዓባልና ሌሎች በዚሁ ደንብ በሚዘረዘሩ ተሳታፊዎች የሚመሰረት፣ በየአመቱ የሚሰበሰብ፣ ከፓርቲው አጠቃላይ ጉባኤ ቀጥሎ የፓርቲው ከፍተኛ የሥልጣን አካል ነው።

3.3. የወረዳ የፓርቲ ጉባኤ፣ የታችኛው የፓርቲው ዝቅተኛ አሃድ በምርጫ ክልል/ወረዳ ደረጃ የተሰባሰቡ አባላት የሚመሰርቱት የ..... ፓርቲ የምርጫ ክልል/ወረዳ በመባል የሚታወቅ የምርጫ ክልል/ወረዳ መዋቅር ከፍተኛ አካል ነው። የወረዳው ዝርዝር መዋቅርና አሰራር ከዞን ከክልልና ከሀገራዊ መዋቅር በተጣጠመ መልኩ በብሥአኮ ተጠንቶ በሥራ ላይ የሚውል ይሆናል።

3.4. ብሄራዊ የህግ ተርጓሚና አስፈፃሚ ኮሚቴ/ብህተአኮ/፡-የፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ ተርጓሚና የስነርአትና የዲስፕሊን የግልግል ስራ የማከናውን ሃላፊነት ያለውና በጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጡ አባላት ያሉት፣ ብሄራዊ ህገ-ደንብ ተርጓሚና ወሳኝ ኮሚቴ (ከዚህ በኋላ ብህተአኮ በመባል የሚታወቅ) ይኖረዋል፣

3.5. የውጭ አዲተር፡- በምርጫ ህጉ መሰረት የፓርቲ አባል ያልሆኑ በውድድር የሚመረጡ የኦዲት ሙያ አገልግሎት የሚሰጡና ለብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ/ብሥአኮ/ ሪፖርት የሚያደርጉ አካላት ናቸው።

3.6. የፓርቲው የውስጥ አዲተር፡-በፓርቲው ጠቅላላ ጉባዔ የሚሰየሙ የፓርቲ አባላት የሆኑ አዲተሮች የኦዲት ሙያ አገልግሎት የሚሰጡ ለጠቅላላ ጉባዔ ሪፖርት የሚያደርጉ አካላት ናቸው።

3.7. ብሄራዊ የፓርቲ አመራር፣ በፌድራልና በክልል የሥራ አስፈጻሚ አካላትና ም/ቤቶች ውስጥ የሚኖረው ሥራ በበላይነት የሚያስተባብር አካል ነው፣

3.8. የብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ/ብሥአኮ/፡- የሃገራዊ ፓርቲውን አጠቃላይ የቀን ተቀን ስራ የሚያስተባብርና የሚመራ በጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጡ አባላት የተካተቱበት (ከዚህ በኋላ ብሥአኮ በመባል የሚታወቅ) የፓርቲ አካል ነው።

3.9. ብሄራዊ የባጀትና የፋይናንስ ኮሚቴ፣

3.10. ብሄራዊ የፖሊሲ አፍላቂ ኮሚቴ፣

3.11. ብሄራዊ የሕዝብ ግንኙነት ኮሚቴ፣

3.12. ብሄራዊ የድርጅት ጉዳይ ኮሚቴ፣

3.13. የፓርቲ ዋና ጸሀፊ፣

3.14. ብሄራዊ የወጣቶች ጉዳይ ኮሚቴ፣

3.15. ብሄራዊ የሴቶች ጉዳይ ኮሚቴ፣

3.16. ብሄራዊ የሙያ ማህበራት ጉዳይ ኮሚቴ፣

3.17. የፓርቲው የውጭ ክንፍ ኮሚቴ፣ በውጭ በሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን የሚያደራጅ የፓርቲ አካል ነው።

DRAFT


ብሔራዊ ጠቅላላ ጉባኤ
ብሔራዊ የፓርቲ ኮንፍረንስ
ብሔራዊ የሕግ ተርጓሚ ኮሚቴ
የኦዲት ኮሚቴ
የኮንፍረንስ አዘጋጅ ኮሚቴ
የክልል ኮንፍረንስ
ብሔራዊ የፓርቲ መሪ
መሪ እና ምክትል
ብሔራዊ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ
ሊቀመንር
የዞን የፓርቲ አካል
ብሔራዊ የአስፈጻሚ ቅርንጫፍ (መንግሥት ወይንም ጥላ መንግሥት)
የሕዝብ ተወካዮች
የፌዴሬሽን ምክር ቤት
የክልል የፓርቲ መሪዎች ስብስብ
ብሔራዊ የንግዘብ እና ቢጅት ንንዘብ ያዥ
ብሔራዊ የፖሊሲ ስትራንግ ኮሚቴ
የወረዳ ጠቅላላ ጉባኤ
የክልል 1 የፓርቲ መሪዎች
የስዝብ ግንኙነት እና ኮሙኒኬሽን
የክልል 2 የፓርቲ መሪዎች
የክልል ሥራ አስፈጻሚዎች ስብስብ (የአሥረጂጀት ጉዳይ)
ዋና መሥሪያ ቤት የጽሕፈት ቤት ኃላፊ
ብሔራዊ ውጣት ማኅበራዊ ጻምክራዮች
ብሔራዊ ቤት ማኅበራዊ ጻምክራዮች
ብሔራዊ የሠራተቾ ማኅበራት ግብኙነት
በውም የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ጸእ
የክልል ... የፓርቲ መሪዎች
የክልል 9 የፓርቲ መሪዎች
የሊቪስ እና መራጩች ብብት
የፖለቲካ ጥናት እና ምርምር
የአመራር ማብቂያ ብቋም

DRAFT

ምዕራፍ III፡ የፓርቲው ድርጅታዊ ዋና ዋና አካላት፣

አንቀፅ 4፡ የፓርቲው ጠቅላላ ጉባዔ፣

4.1. የጠቅላላ ጉባዔ አባላት

ጠቅላላ ጉባዔው የፓርቲው ከፍተኛ የስልጣን አካል ሲሆን ቁጥራቸው እስከ 2000 የሚደረስ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል።

4.1.1. ፓርቲው መዋቅር ከዘረጋባቸው የምርጫ ክልሎች የሚወከሉ በድምፅና ያለ ድምጽ የሚሳተፉ አባላት (ያለ ድምፅ የሚሳተፉ አባላት ቁጥር በብሔራዊ ምክር ቤቱ የሚወሰን ይሆናል) ይኖሩታል። የጉባኤተኞች አመራረጥ የጾታ ተዋጽዖን ግምት ወስጥ ያስገባ ይሆናል።

4.1.2. የብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት፣

4.1.3. የብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚወክላቸው በምርጫ ክልል ውክልና ያላገኙ የፓርቲው ንቁ ተሳታፊዎች ቁጥራቸው ከሃያ የማይበልጥ ሆኖ፣ በዚህ ሁኔታ ወደ ጉባዔ የሚመጡ ዓባላት በጉባዔ ለሚደረጉ ምርጫዎች ዕጩ ሆነው አይቀርቡም።

4.1.4. የምርጫ ወረዳዎች የምክር ቤት ተመራጭ ተወካዮች፣

4.1.5. የፓርቲው የፌዴራልና የክልል ፓርላማ ተመራጮች፣

4.1.6. ፓርቲው በምርጫ የሚሰይማቸው ወይም ለምርጫ የሚያቀርባቸው እጩ ከንቲባዎች፣ ወይም ሌሎች ሹመኞች፣

4.1.7. የብሄራዊ ፖሊሲ ኮሚቴ አባላት፣

4.1.8. ከ ..... ፓርቲ አለም አቀፍ በአህጉር 2 ተወካዮችን ይልካሉ፣

4.1.9. የፓርቲው አዲተሮች አባላት፣

4.1.10. የብህተአኮ አባላት፣

4.1.11. ወደ ጉባኤ የሚላኩና በጉባኤ የሚሳተፉ አባላት ፓርቲው ለአባላት ያሰቀመጠውን የአባልነት ግዴታቸውን ያሟሉ መሆናቸውን እያንዳንዱ ለጉባኤ ተወካይ የሚልክ አካል ማረጋገጥ ይኖርበታል። ይህን በማያደርጉ አካላት ላይ ብሥአኮ የስነስርአት እርምጃ ይወስዳል።

4.2. የፓርቲው ጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር፣

4.2.1. አጠቃላይ የፓርቲ ጉባኤ የፓርቲው የመጨረሻው የስልጣን እርከን ነው።

4.2.2. ጠቅላላ ጉባኤ በ ሦስት ዓመት አንድ ጊዜ ይስበሰባል።
4.2.3. የፓርቲ ጉባኤ ተግባራቱን የሚያከናውነው በድርጅቱ የመተዳደሪያ ደንብና ሌሎች ጠቅላላ ጉባኤው ባስተላለፋቸው ቋሚ መመሪያዎች አማካይነት ይሆናል።
4.2.4. የፓርቲው መሪ የሚያቀርበውን ከሃገሪቱና ከፓርቲው የፓርላማ እንቀስቃሴ ጋር የተያያዙ ሪፖርቶችን ያዳምጣል። ያጸድቅል።
4.2.5. የፓርቲው ሊቀመንበር ስለፓርቲው የሚያቀርበውን የስራ ሪፖርት ያደምጣል። ያጸድቃል።
4.2.6. በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ወቅታቸውን ጠብቀው በጠቅላላ ጉባኤ መደረግ የሚገባቸውን ምርጫዎች ያከናውናል።
4.2.7. የፓርቲው ስያሜ፣ ፕሮግራምና ደንብና ያጸድቃል፣ ያሻሽላል፣ ይሽራል።
4.2.8. ከኡዲተር የሚቀርብለትን የኡዲት ሪፖርት መርምሮ ያፀድቃል።
4.2.9. ከህተአኮ የሚቀርብለትን ሪፖርት መመምሮ ያፀድቃል።
4.2.10. ፓርቲውን በሚመለከቱ በማናቸውም ሌሎች ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ ይሰጣል።
4.2.11. የጠቅላላ ጉባዔ የድምፅና ውሳኔ አሰጣጥ በሌሎች አንቀፆች በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር በአብላጫ ድምፅ (50+1%) ይሆናል።
4.2.12. ብሥአኮ አሰፈላጊ ሆኖ ካገኘው አስቸኳይ የፓርቲ ኮንፈንስ መጥራት ይችላል። የብሥአኮ አባለት በሁለት ሶስተኛ ድምፅ ጉባዔ እንዲጠራ ወስነው የፓርቲው ሊቀመንር ጉባኤ ለመጥራት ፈቃደኛ ካልሆነ ጥያቄያቸውን ለህተአኮ በማቅረብ እንዲጠራላቸው ማድረግ ይችላሉ።

አንቀፅ 5. የፓርቲ ኮንፈረንስ፣

5.1 የፓርቲ ኮንፈረስ ዓባላት፣

ከፓርቲው ጠቅላላ ጉባዔ ቀጥሎ የፓርቲው ከፍተኛ የስልጣን አካል ሲሆን የሚከተሉት ዓባላት ይኖሩታል፣

5.1.1 እያንዳዳቸው ፓርቲው መዋቅር የዘረጋባቸው የምርጫ ክልሎች የምትወከል ድምጽ የምትሰጥ (የሚወከል ድምጽ የሚሰጥ) አንድ ዓባል፣

5.1.2 በጠቅላላ ጉባኤ የሚሳተፉ ሌሎች አካላት በሙሉ፣

5.2 የፓርቲው ኮንፈረስ ሥልጣንና ተግባር፣

5.2.1 ኮንፈረንሱ በጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጡ ሰባስቢ፣ ም/ሰብሳቢና ጸሀፊ ይኖረዋል፣
5.2.2 የፓርቲውን ጠቅላላ ገባኤ ወክሎ የፓርቲውን እንቀስቃሴ ይመራል፣
5.2.3 የኡዲትና የህግ ኮሚቴ ሪፖርቶችን ያዳምጣል፣ መመሪያ ይሰጣል ፣
5.2.4የሥራ አስፈጻሚ እና የፓርቲ አመራር አመታዊ የስራ ዘገባና እንቅስቃሴ ይገመግማል፣
5.2.5 የፖሊሲ ረቂቅ ያጸድቃል፣
5.2.6 የፋይናንስ ሪፖርት ያዳምጣል፣ አመታዊ ባጀት ያጸድቃል፣

DRAFT

5.2.7 የህገደንብ ማሻሻያወችን በጊዜያዊነት ያጸድቃል፣

5.2.6 በጠቅላላ ጉባኤ ተመርጠው ለጎደሉ ቦታዎች ተተኪ አባላትን ይመርጣል፣

5.2.7 ዓመታዊ ስብሰባ ያካሂዳል፣

አንቀጽ 6 ብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ

6.1 የብሔርዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት

በፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጡ እና በተመራጭ የፓርቲው ሊቀመንበርና ምክትል ሊቀመንበር በምክክር የሚሰየሙ አባላት ያሉት በፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ ቁጥጥርና መመሪያ የሚሰራ ፓርቲውን የማስተዳደር ስልጣን ያለው ብሄራዊ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ (ብሥአኮ) ይኖራል።

6.1.1 የፓርቲው መሪ/ ከፓርላማ ተመራጮች፣
6.1.2 የፓርቲው ምክትል መሪ/ከፓርላማ ተመራጮች፣
6.1.3 የመንግስት/ትይዩ ካቢኔ ተወካዮች(3)፣
6.1.4 የፓርላማ አባላት ተወካይ፣
6.1.5 የፌዴሬሺን ምክር ቤት አባላት ተወካይ፣
6.1.6 የፓርቲው ሊቀመንበር፣
6.1.7 የፓርቲው ምክትል ሊቀመንበር (የክልል ፓርቲ ሊቃነመናብርት ስብስብ መሪ)፣
6.1.8 የፓርቲው ዋና ፀኃፊ፣
6.1.9 የፓርቲው ባጀትና ፋይናንስ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ /ትሬዝረር፣
6.1.10 የፓርቲው ህዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፣
6.1.11 የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ሰብሳቢ፣
6.1.12 የወጣቶች ጉዳይ ተጠሪ(2)፣
6.1.13 የሴቶች ጉዳይ ተጠሪ(2)፣
6.1.14 የሙያ ማህበራት ግንኙነት ተጠሪ(2)፣
6.1.15 የዓለም አቀፍ አባላት ተጠሪ፣

6.2 የብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር፣

DRAFT

በብሔራዊ ምክር ቤት በሚወጣ ዝርዝር መመሪያ መሰረት ተግባሩን የሚከውን በጠቅላላ ጉባኤ የሚሰየም ዐዐዐ አባላት ያሉት ኮሚቴ ይሆናል። የብሥአኮ ዋናው ተግባር ለፓርቲው ስትራተጂክ አመራር መስጠት፣ ከፓርቲው የተለያዩ አካላት ጋር በመቀናጀት ቀልጣፋ ንቁ ሃገራዊ ፓርቲ በፓርማ በክልልና ወረዳ ምክር ቤቶች እንዲኖር ማድረግ ነው። ሲዘረዘር

6.2.1 ለፓርቲው ፖሊሲዎች መዳበር አስተዋጸኦ ማድረግ፣
6.2.2 ምርጫ ማሸነፍና የመራጮችን ድጋፍ በቀጣይነት ማሳደግ፣
6.2.3 በሁሉም የፓርቲው እርከኖች የፓርቲውን ጤንነት መጠበቅ፣ አባላት በማህበረሰቡ በአርአያነት የሚያዩበት ሰብአዊና የበለጸገ ባህል እንዲኖራቸው ማድረግ፣
6.2.4 የፓርቲ አባላት ከፓርቲው የሚያገኙትን ማንኛውም አገልግሎት፣ ከፓርቲ አባላት ጋር በሚገባ ውል መሰረት፣ ፈጣንና ቀልጣፋ ማድረግ፣
6.2.5 የፓርቲውን ተግባራዊ ሃላፊነቶችና እና የፓርቲው ህግ የጣለበትን ግዴታዎች በሚገባ ማሟላት፣
6.2.6 በተለያዩ የፓርቲው አካላት መሃል ቀጣይነት ያለው ሚዛናዊ የባለቤትነት ስሜትና ግንኙነት እንዲኖር ማድረግ፣
6.2.7 የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንቦች፣ ፓርቲው በተለያዩ ወቅቶች ያሳለፋቸውን ወሳኔዎች መመሪያዎች በሚጥሱ የፓርቲው አባል፣ አሃድ፣ ወይም የተቆራኘ ማህበር ላይ በፓርቲው የስነስርአት አወሳደድ ደንብ መሰረት እርምጃዎችን መውሰድ፤
6.2.8 የተለያዩ የፓርቲው አምዶች በሚገባ መደራጀታቸውንና የሰራ እንቅስቃሴ ማድረጋቸውን ማረጋጋጥ፤
6.2.9 ከፓርቲው የፖሊሲ ፎረም ጋር ተደጋግፎ መስራት የሚያስችለውን የጋራ የፖሊሲ ኮሚቴ በማቆም ኮሚቴው ስራውን በሚገባ ማከናወኑን ማረጋገጥ፣
6.2.10 ፓርቲው በምርጫ ወረዳና ከዛም በታች ከምርጫ ማስፈጸም ጋር የተገናኘና ለዚህ ስራ ተብሎ የተደራጀ የከባቢ የምርጫ ፎረሞች እንዲቋቋሙና በሚገባ እንዲሰሩ ማድረግ፤
6.2.11 ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው የማህበረሰብ ክፍሎች፣ በተለይ የሴቶችና የወጣቶች የፓርቲው አባላት ማህበራት በየወረዳው እንዲመሰረቱና ሃገር አቀፍ አደረጃጀት እንዲኖራቸው ማድረግ፣
6.2.12 ፓርቲው በእድሜ፣ በጾታ፣ በአካል ጉዳተኝነት፣ በእምነት እና በዘር/በብሄር ምንም አይነት ልዩነት የማያደርግ፣ ማንንም የማያገል፣ ለሁሉም ዜጎች በነጻነት መሳተፍ ክፍት የሆነ መሆኑን በቀጣይነት ማረጋገጥ፤
6.2.13 የፓርቲውን የፋይናንስ አቅም ለማጎለበት የሚያስችሉ በእቅድ የሚመሩ የገንዘብ የቁሳቁስ ማሰባሰቢያ ስራዎች ተግባራዊ ማድረግ፣
6.2.14 በሁሉም ደረጃ የሚደረጉ የፓርቲ ጉባኤዎች ዴሞክራሲያዊ የሆኑ የስብሰባ ስርአቶችን የተከተሉ፣ በመተሳሰብ ቤተሰባዊ ስሜት የተሞሉ፣ የብዙሃኑን ተሳታፊነት የሚያበረታቱ፣ በሚገባ ዝግጅት የተደረገባቸው ስሉጥና ቀልጣፋ እንዲሆኑ ማድረግ፣
6.2.15 በፓርቲ አባላት እንዲሁም ከፓርቲው ጋር ግንኙነት ባላቸው አካላት መሃል የሚከሰቱ ልዩነቶች ላይ ዳኝነት መስጠት፣
6.2.16 ፓርቲው ማናቸውንም የፋይናንንስ ሃላፊነቶችና የሃገሪቱ ህግ የጣለበትን ሃልፊነቶችና ግዴታዎች በሚገባ እንዲወጣ ማድረግ፣
6.2.17 በፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ ውይይት ሊደረግባቸውና ሊጸድቁ የሚገባቸውን ማናቸውንም ለፓርቲው እንቀሰቃሴና እድገት የሚጠቅሙ መመሪያዎች ደንቦች፣ ፖሊሲዎችና ሌሎችንም ጉዳዮች በተደራጀ መንገድ ለጉባኤ ውሳኔ ማቅረብ፤
6.2.18 በቋሚነት በሚደረገው አመታዊ የፓርቲው ጉባኤ የፓርቲውን የስራና በሚገባ አዲት የተደረገ የፋይናንስ ዘገባ ለጉባኤተኞች ማቅረብ፣
6.2.19 የብሄራዊ የስራ አሰፈጻሚ ኮሚቴ አሰፈላጊ ሆኖ ካገኘው ስልጣኑንና ስራውን በክልል በሌሎችም እርከኖች፣ ስልጣንና ሃላፊነት በሚሰጣቸውና በስሙ በሚንቀሳቀሱ ተወካዮች አማካይነት የማስፈጸም ሙሉ መብት አለው።

አንቀፅ 7፡ የብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ አባላት ሥልጣንና ተግባር/ የጉባዔ ተመራጮች፡

7.1 የፓርቲው መሪ

7.1.1 የፓርቲው የፓርላማ አባላት ቁጥር 30 በሚደርስበት ወቅት የፓርቲው መሪና ምክትል መሪ ሆነው የሚመረጡት ግለሰቦች የሚጠቆሙት በፓርላማ አባላትና ከፓርላማው አባላት መሃከል ይሆናል። ለፓርቲ መሪነት ዕጩ ሆኖ የተጠቆመ ምክትሉን ይዞ ለውድድር ይቀርባል።
7.1.2 የፓርቲው መሪና ምክትል መሪ በሁሉም የፓርቲው አባላት "በአንድ ሰው አንድ ድምጽ የምርጫ መርህ በቀጥታ ይመረጣሉ።
7.1.3 የፓርቲው መሪና ምክትል መሪ የአጠቃላይ የፓርቲው መሪና ምክትል መሪ ናቸው።
7.1.4 የፓርቲው መሪና ምክትል መሪ የፓርቲውን የቀን ተቀን ስራ የሚመራው የብሥአኮ ሊቀመንበርና ምክትል ሊቀመንበር ሆነው መመረጥ አይችሉም።

7.1.5 የፓርቲው መሪ ወይም መሪው በራሱ ምትክ የወከለው ግለሰብ ማንኛውንም የፓርቲ ስብሰባ የመሳተፍ መብት አለው።

7.1.6 መሪው የብሄራዊ ስራ አስፈጻሚ ከሚቴ አባል ነው። የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብና ሌሎችንም የፓርቲውን ቋሚ መመሪያዎች የማስከበር ሃላፊነትና ፓርቲውን በፓርላማና በሀገር ደረጃ ቀልጣፋና የተሳለጠ የማድረግ ሃላፊነት አለበት።

7.1.7 የፓርቲው መሪ በጉባኤ ወቅትና በጉባኤዎች መሃከል ለጠቅላላ ጉባኤ፣ ለብሥአኮ፣ ለብሄራዊ ፖሊሲ ፎረምና ለሌሎችም የፓርቲው አካላት ወቅታዊ የሃገርና የፓርቲውን ሁኔታ የተመለከተ ዘገባዎችን ያቀርባል።

7.1.8 መሪው ከብሄራዊ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ጋር በመሆን ከምርጫ ጋር የተሳሰሩ ሃላፊነቶችን በሙሉ ይወስዳል፣ የምርጫ ዘመቻ አስተባባሪ እና የምርጫ ኮሚቴ አባላትን ይሰይማል፣ የምርጫው ዘመቻ ሪፖርቶችን እንዲደርሰው ያደርጋል፣ የምርጫ ዘመቻ ኮሚቴዎች የሚያስፈልጋቸውን ትብብርና ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል።

7.1.9 ፓርቲው ስልጣን ከያዘ መሪው ጠቅላይ ሚኒስቴር ይሆናል። በጠቅላይ ሚኒስትርነቱ የካቢኔ አባላቱንና ሌሎችንም በሹመት የሚያዙ የሚኒስቴር ስልጣኖችንና የፓርቲውን የፓርላማ ሃላፊዎችን ይሰይማል፣

7.1.10 ፓርቲው ስልጣን ላይ ካልወጣ መሪው ዋና ወይም ዋና ያለሆነ የፓርላማ ተቃዋሚ ፓርቲ መሪ ይሆናል። ከዚህ ስልጣኑ ጋር ተያይዞ የትይዩ የካቢኔ አባላቱንና ሌሎችንም የትይዩ ሚኒስትሮችና የተለያዩ የፓርቲውን የፓርላማ ሃላፊዎችን ይሰይማል፣

7.1.11 መሪው በቋሚነት ምክትል መሪውን እያማከረ ይሰራል፣ የፓርቲው ተልእኮ እንዲሳካ ምክትሉ ለመሪው ምክር ይለግሳል መሪው በጠየቀው ወቅት ቦታ በእንደራሴነት ያገለግላል።

7.1.12 የፓርቲው መሪ ፓርቲው ሥልጣን ከያዘ ከሁለት ተከታታይ የፓርላማ ዘመን በላይ ማገልገል አይችልም።

7.2 የፓርቲው ምክትል መሪ፣

7.2.1.1 የፓርቲው ምክትል መሪ ከላይ በተገፀው መሰረት ይመረጣል።

7.2.1.2 ምክትል መሪው የብሄራዊ ስራ አስፈጻሚ ከሚቴ አባል ነው።

7.2.1.3 የፓርቲው ምክትል መሪ የፓርቲው መሪ በተሰጠው ሃላፊነት ዋንኛ ኣጋር ሆኖ ይሰራል።

7.2.1.4 መሪው በሌለበት ወቅት ያለምንም ተጨማሪ ውክልና ተክቶ ይሰራል።

7.2.1.5 ሌሎች በመሪው የሚሰጠውን ሃላፊነትና ተግባራት ያከናውናል።

7.3 የፓርቲው ሊቀመንበር፣

7.3.1 የፓርቲው ሊቀመንበር መስፈርት አሟልቶ ከቀረቡ ዕጩዎች መካከል በጉባዔ ይመረጣል። የስልጣን ዘመኑ ሶስት ዓመት ሲሆን፣ ሊቀመንበሩ ከሁለት ምርጫ ዘመን በላይ ማገልገል አይችልም። ሊቀመንበሩ አብሮት የሚሰራውን ምክትል ሊቀመንበር ዕጩ ይዞ በመቅረብ በጣምራ ይመረጣሉ።

7.3.2 የፓርቲው ሊቀመንበር ከፓርቲው የፓርላማ መሪና ምክትል መሪ የሚለዩ የፓርቲውን የቀን ተቀን ተግባራት በሙሉ ጊዚ የሚመራ ሰለሆነ፣ የፓርላማ አባል ሆኖ መመረጥ አይችልም።

7.3.3 በአመት ወስጥ የሚደረጉ የጠቅላላ ጉባኤና ሊሎችንም ስብሰባዎችን በሃላፊነት ይመራል።

7.3.4 ፓርቲው በጠቅላላ ጉባኤ የወሰናቸው ውሳኔዎችናና ያስተላላፋቸው መመሪያዎች መከበራቸውንና በተግባር መፈጸማቸውን ይቆጣጠራል።

7.3.5 ማናቸውንም በየትኛውም እርከን የሚከናወን የፓርቲውን ሃገር አቀፍ የቀን ተቀን እንቅስቃሴ በሃላፊነት ይመራል።

7.3.6 በጉባዔ ከተመረጡ የብሥአኮ አባላት ውጭ ያሉትን አባላት ከምክትሉና በጉባኤ ተመራጭ ከሆኑ የብሥአኮ አባላት ጋር በመመካከር ይመድባል።

7.4 የፓርቲው ም/ሊቀመንበር፣

ምክትል ሊቀመንበሩ ከፓርቲው ሊቀመንበር ጋር በጣምራ በዕጩነት ቀርቦ ይመረጣል። ተጠሪነቱ ለብሥአኮ እና ለሊቀመንበሩ ይሆናል። የስልጣን ዘመኑ 3 አመት ይሆናል።

7.4.1የፓርቲው ምክትል ሊቀመንበር የፓርቲውን የቀን ተቀን ተግባራት በሙሉ ጊዜው ከፓርቲው ሊቀመንበር ጋር የሚመሩ ሰለሆነ፣ የፓርላማ አባል ሆነው መመረጥ አይችሉም።

7.4.2 ለፓርቲው ሊቀመንበር የተሰጠውን ሃላፊነት በጋራ ይወጣሉ።

7.4.3 የፓርተው ሊቀመንበር በማይኖርበት ወቅት ያለምንም ተጨማሪ ውክልና ተክቶ ይሰራል።

7.4.4 በፓርቲው ሊቀመንበር ተለይቶ የሚሰጠውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

7.4.5

7.5 የፓርቲ ዋና ፀሃፊ፣

የፓርቲው ዋና ፀኃፊ የፓርቲው ብሥአኮ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ለእጩነት ቀርቦ በፓርቲው ጠቅላላ ጉባዔ የሚመረጥ ይሆናል። ተጠሪቱ ለብሥኮና ለሊቀመንበሩ ይሆናል።

7.5.1.1 የፓርቲው ጸሃፊ ሙሉ ጊዜውን በፓርቲ ስራ ላይ መዋል ያለበት በመሆኑ ለፓርላማ ወድድር መቅረብ አይችልም።

7.5.1.2 ጸሃፊው ጠቅላላ ጉባኤውንና ብሥአኮን በስራው ማርካት እስከቻለ ድረስ በተደጋጋሚ መመረጥ ይችላል።

7.5.1.3 ጸሃፊው ስራ በሚለቅበት ወይም ቦታው በተለያዩ ምክንያቶች የጸሃፊነቱ ቦታ ባዶ ከሆነ ብሥአኮ ሌላ ጸሃፊ በቦታው ተክቶ ማስራት ይችላል። ተተኪው ጸሃፊ በቀጣዩ የፓርቲው አጠቃላይ ጉባኤ ተቀባይነት ማግኘት አለበት።

7.5.1.4 የፓርቲውን የድርጅት ጉዳይ ይመራል፣ የምርጫ ወረዳ አደረጃጀቶችን ቀልጠፋ በሆነ መንገድ ለመምራት የሚያስችል አደረጃጀት በብሥአኮ ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል።

7.5.1.5 ዋና ጸሃፊው የብሥአኮም ጸሃፊ ይሆናል።

7.5.1.6 ፓርቲው የሚገለገልባቸውን የሥራ መመሪያዎች፣ የፋይናንስ ሥርዓት፣ ወዘተ እንዲዘጋጅ በማድረግ በብሥአኮ ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል።

7.6 ፋይናንስ/ትሬዝረር፣

የፓርቲው የፋይናንስ/ትሬዝረር ብሥአኮ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ለእጩነት ተጠቁሞ በጉባዔ ይመረጣል። ተጠሪነቱ ለብሥአኮና ለሊቀመንበሩ ይሆናል።

7.6.1የፓርቲው ብሥአኮ አባል ሆኖ ያገለግላል።

7.6.2 የፓርቲውን የፋይናንስ ሥርዓት ዓለም አቀፍ ደረጃዎች ያሟላ ተጠያቂነትን በሚያረጋገጥ ሁኔታ መሆኑን ያረጋግጣል።

7.6.3 የፓርቲው ፋይናንስና ንብረት በአግባቡ መጠበቁን እና ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል።

7.6.4 የፓርቲው ሠነዶች በማንኛውም ጊዜ ለኡዲት ሥራ ዝግጁ እንዲሆኑ ክትትል ያደርጋል።

7.7 ሌሎች

ሌሎች ብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ሥልጣንና ተግባር በብሥአኮ የሚዘጋጅና የሚፀድቅ ይሆናል።

አንቀፅ 8፡ ብሄራዊ የፓርቲ አመራር፣

8.1 ብሄራዊ የፓርቲ አመራር አካል፣

8.1.1 በምርጫ ክልል/ወረዳ የተመረጡ የፌዴራል ምክር ቤት አባላት በሙሉ የፓርላማ ቡድን አባላት ናቸው።

8.1.2 በምርጫ ክልል/ወረዳ በመወከል የተመረጡ የክልል ምክር ቤት አባላት የክልል ምክር ቤት አባላት ማሕበር ያቋቁማሉ።

DRAFT

8.2 የብሄራዊ የፓርቲ አመረር ሥልጣንና ተግባር፣

8.2.1 በፓርላማና በሌሎች ምክር ቤቶች ውስጥ ፓርቲውን ወክለው ይሰራሉ።

8.2.2 በፌደራል ፓርላማና በለሎች ምክርቤቶች የተመረጡ የፓርቲው ተወካዮች በሰየሙት መሪና ምክትል መሪ አማካይነት የፓርቲውን እንቅስቃሴ በመከታተል በምክር ቤት ውስጥ የፓርቲውን ውክልና ያሳልጣሉ።

8.2.3 የፌደራል ፓርላማ ተመራጮች የፓርቲውን መሪና ምክትል መሪ ዕጩዎች በማቅረብ በጠቅላላ የፓርቲው አባላት እንዲመረጡ ያደርጋል።

8.2.4 ሁሉም የፌዴራል ፓርላማ አባላት በጠቅላላ ጉባዔ የመሳተፍ መብት አላቸው።

8.2.5 በፓርቲው የፌደራል ፓርላማና የምክር ቤት መሪዎች የሚሰየሙ ሻዶ ካቢኔዎችን ሥራ ይቆጣጠራሉ።

አንቀፅ 9፡ ኦዲተር፣

9.1 ፓርቲው የፋይንናስ እና ክዋኔ ኦዲት ሞያ ያላቸው ሁለት ኦዲተሮች ይሾማል። በተጨማሪ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባዔ የሆነ ለሶስት ዓመት አገልግሎት የሚሰጥ ባለሞያ የውጭ ኦዲተር ይሾማል።

9.2 ከኦዲተሮቹ አንዱ ወይም ሁለቱ ቢጎድሉ በኦዲተሮች ምርጫ በቅደም ተከተል ከፍተኛ ድምጽ አግኝተው የነበሩ እጩዎች በቦታቸው ይተካሉ። ይህ የሚሆነው እስከሚቀጥለው የፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ ድረስ ብቻ ነው።

9.3 የሚመረጡት የኦዲት አባላት በፓርቲው የየትኛውም መዋቅር ከገንዘብ ጋር ተያያዥነት ያለው ሃላፊነት ያላቸው መሆን አይችሉም

9.4 ተግባራቸው የፓርቲውን አካዎንትና የፋይናንስ ስርአት መቆጠጠርና ለጠቅላላ ጉባኤ ሪፖርት ማድረግ ይሆናል።

9.5 የፓርቲ ኦዲተሮች የሥራ ዘመን ሶሰት ዓመት ነው።

አንቀፅ 10፡ የደንብ ተርጓሚና ዲሲፕሊን ኮሚቴ፣

10.1 የደንብ ተርጓሚና ዲሲፕሊን ኮሚቴ አባላት፣

10.1.1 ቁጥራቸው .....5.... የሆኑ በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡ አባላት ይኖሩታል።

10.1.2 የኮሚቴው እጩ አባላት ጥቆማ ጠቅላል ጉባኤ ባጸደቀው ድንብ መሰረት ይከናወናል።

10.1.3 የብህተወኮ አባላት ከፓርቲው የምርጫ ወረዳ አምዶች በየክልሉ ይመረጣሉ።

10.1.4 የብህተወኮ አባላት የአገልግሎት ዘመን 3 አመት ይሆናል።

10.2 የደንብ ተርጓሚና ዲሲፕሊን ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር፣

10.2.1 በፓርቲው መዋቅሮች የቀረበለትን ከሰነስራት ጋር የተያያዘ ጉዳይ ይመለከታል።

DRAFT

10.2.2 በብሄራዊ የስራ አሰፈጻሚ ኮሚቴ የቀረበለትን ከስነስርዓት ጋር የተያያዘ ጉዳይ ይመለከታል።

10.2.3 በፓርቲ መዋቅሮች አምዶች ይሁን በብሥአኮ የስነስርአት ውሳኔ በተሰጠባቸውና በቀረቡለት የስነስርአት ጉዳዮችን መርምሮ ቅጣት የማጽደቅና ቅጣት የማሻሻል ስልጣን ይኖረዋል።

10.2.4 በፓርቲ መዋቅሮች ይሁን በብሥአኮ የስነስርአት ውሳኔ ሳይሰጥባቸው በቀረቡለት የስነስርአት ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል።

10.2.5 በህተአኮ የሰጠው ውሳኔ ግዥና የመጨረሻ ይሆናል።

10.2.6 የፓርቲው ሊቀመንበር የጠቅላላ ጉባዔ ለመጥራት ፈቃደኛ ካልሆነ እና ሁለት ሶስተኛ የብሥአኮ አባላት ወይም ሶስት አራተኛ የፓርቲው አምዶች በአብላጫ ድምፅ የደገፉትን የጉባዔ ይጠራልን ጥያቄ መሰረት አድርጎ ጉባኤ ይጠራል።

ምዕራፍ IV፡ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አንቀፅ 11. ኤዲቶሪያል ቦርድ፣

በፓርቲው ጠቅላላ ጉባዔ በሚፀድቅ የውስጥ ደንብ የሚተዳደር ከብሥአኮ ነፃ የሆነ የኤዲቶሪያል ቦርድ ይቋቋማል። አባላቱን ዝርዝርና ሥልጣንና ተግባሩ በውሥጥ ደንብ ይወሰናል።

አንቀፅ 12. የፓርቲው ፅ/ቤት፣

የፓርቲው ዋና ፅ/ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ሲሆን እንዳስፈላጊነቱ በማንኛውም የሀገሪቱ ክፍል እና በውጭ ሀገራት ፅ/ቤቶችን ይከፍታል። የምርጫ ክልል/ወረዳ ፅ/ቤቶች የሚከፈቱት በምርጫ ክልል/ወረዳ የፓርቲ አባላት የሚፈለገውን መመዘኛ ማሟላታቸው ሲረጋገጥ ከብሥአኮ በሚሰጥ እውቅና መሰረት ይሆናል። ፓርቲው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የማሰተባበሪያ ፅ/በቶች በአገሪቱ ውስጥ ቦዞን፣ በቀጣና ወይም በሌላ መስፈርት የሚከፍት ይሆናል።

አንቀፅ 13፡ አባልነት።

የፓርቲውን ደንብ ፕሮግራም የተቀበለ፣ በፓርቲው የሥነ ምግባር ደንብ መሰረት ለመተዳደር ፈቃደኛ የሆነ እድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ ኢትዮጵያዊ የፓርቲ አባል መሆን ይችላል። የፓርቲ ሙሉ አባል ለመሆን እና የአባልነት መብትን ለመጠቀም በዕጩ አባልነት መቆየትና በነዋሪነት በተመዘገበበት የምርጫ ክልል/ወረዳ ተቀባይነት ማግኘት ይኖርበታል። ማንኛውም የፓርቲ አባል በምርጫክልል/ወረዳ ተደራጅቶ ለመንቀሳቀስ ፈቃደኛ መሆን ይኖርበታል።

DRAFT

13.1 ዕጩ አባል፣

13.1.1የፓርቲው ዕጩ ለመሆን በቅድሚያ ፓርቲው በሚያዘጋጀው የተለያየ የደጋፊ አባላት መሳተፍና የደጋፊ አባልነት ግዴታን በአግባቡ መወጣት ያስፈልጋል።

13.1.2 የዕጩ አባል የሚሆነው ማነኛውም ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ፣ የፓርቲውን ፕሮግራምና ደንብ መረዳት የሚቸልና የፓርቲውን ሰነዶች በመቀበል ተግባራዊ ለማድረግ የወሰነ መሆኑ ሲታመንበት ብቻ ነው።

13.1.3 ማነኛውም ዕጩ አባል በዝቅተኛው የፓርቲ መዋቅር ተመዝግቦ ለመሳተፍ፣ ወርሃዊ መዋጮ ለመክፈልና ሌሎች ግዴታዎችን ለመወጣት ፈቃደኛ መሆን ይጠበቅበታል፤

13.1.4 ዴሞክራሲ ለዜጎች ሁሉ እኩል ያስፈልጋል ብሎ የሚያምን በዜጎች መካከል በዘር፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፆታ ወይም በማነኛውም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መመዘኛ ልዩነት የማያደረግ መሆን አለበት።

13.1.5 ፓርቲው የፖለቲካ ስልጣን እንዲይዝ የበኩሉን ድርሻ ለመወጣት ከደጋፊ በላይ ለመሆን የወሰነ እና የፓርቲውን አባልነት መሰፈርት የሚያሟላ መሆኑ የተረጋገጠ ኢትዮጵያዊ ዜጋ የፓርቲው አባል ለመሆን ሲጠይቅ በዕጩ አባልነት ይመዘገባል።

13.1.6 የፓርቲው አባልነት በዋነኝነት የፖለቲካ አመራር ለመስጠት ዝግጁ መሆኑን የሚጠይቅ በመሆኑ በፓርቲው አባልነት ለመሳተፍ የሚያስፈልገውን የአባልነት ምልመላ መስፈርት ዝርዝር መመሪያ ማሟላት ያስፈልጋል። ይህ ዝርዝር መመሪያ በብሔራዊ ስራ አስፈፃሚው ኮሚቴ የሚዘጋጅ ይሆናል።

13.2 ሙሉ አባል፣

13.2.1 ከፓርቲው መስራች ጉባዔ በፊት ተመዝግበው በመስራች አባልነት ዝርዝራቸው ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የተላለፈ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ የአባልነት ግዴታቸውን መወጣት ካላቋረጡ የፓርቲው መስራች አባላት ናቸው።

13.2.2 የፓርቲው እጩ አባል ሆኖ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ እስከ ስድስት ወር መጨረሻ ድረስ የዲስፕሊን ግድፈት ያልተገኘበትና የእጩ አባልነት ግዴታውን በአግባቡ የተወጣ እጩ በምርጫ ክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሲፀድቅ፣ የብሔራዊ ስራ አስፈሚው/ወይም የሚወክለው አካል በመስፈርቱ መሰረት መከናወኑን አምኖበት ሲያረጋግጥ የፓርቲው ሙሉ አባል ይሆናል።

13.2.3 እጩ አባሉ ለሙሉ አባልነት የማያበቃው ግድፈት ሲገኝበት በምርጫ ክልል/ወረዳ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔ የእጩነት ጊዜው ለተጨማሪ 3 ወር ሊራዘም ይችላል። ይህም ሆኖ መሻሻል ካልታየበት ከእጩ አባልነት ይሰረዛል፤ወይም በዕጩ አባልነት እንዲቆይ ሊደረግ ይችላል።

13.2.4 ቀደም ሲል በዕጩ አባልነት ያልተመዘገበ በፓርቲው የብሔራዊ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተጠይቆ አባል ለመሆን ፈቃደኝነቱን የገለፀ ኢትዮጵያዊ በስራ አስፈፃሚው ውሳኔ ሲያገኝ በአንቀፅ 5.1.4. የተመለከተው ተፈፃሚ ሳይሆን የፓርቲው ሙሉ አባል ሊሆን ይችላል። ይህ የሚሆነው ግን አባሉ የፓርቲው አባል ለመሆኑ የወጡትን መስፈርቶች ሙሉ ለሙሉ የሚያሟላ ሲሆን እና ለፓርቲው በተለይ ሁኔታ ይጠቅማል ተብሎ ሲታመንበት ብቻ ነው።

13.2.5 የአባልነት መብት የሚቆየው የአባልነት ግዴታቸውን ለተወጡ አባላት ብቻ ነው።

13.3 ተባባሪ አባል/ደጋፊ፣

13.1.1 በፓርቲው ውስጥ ሙሉ ተሳትፎ ለማድረግ የግል ሁኔታቸው የማይፈቅድላቸው፣ ወይም ደግሞ የፓርቲውን የአባልነት መስፈርት የማያሟሉ ዜጎች በህግ ገደብ ያልተጣለባቸው ከሆነ የፓርቲው ተባባሪ በመሆን ድጋፍ ሊያደርጉ ይችላሉ።

13.1.2 የፓርተው ደጋፊዎች በፓርቲው ውስጥ ኃላፊነት ቦታ ለመመረጥ እና ለመምረጥ እንዲሁም በፓርቲው ውሣኔዎች ላይ ድምፅ ለመሰጠት አይችሉም።

13.1.3 የፓርቲው ደጋፊዎች ምልመላን በተመለከተ ዝርዝር መመሪያ በብሔራዊ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይወጣል።

አንቀፅ 14. የአባልነት መብትና ግዴታ፣

14.1 ማንኛውም አባል፣

14.1.1በፓርቲው ስብሰባዎች ሃሣብ የማቅረብና ድምጽ የመስጠት፣
14.1.2 ፓርቲው የሚያወጣውን መስፈርት በሚያሟላበት የአመራር ቦታ ያለምንም አድሎ የመወዳደር፤
14.1.3 የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብና ፕሮግራም እና ሌሎች መመሪያዎች መከበራቸውን የመከታተል፣
14.1.4 በራሱ ተነሳሽነት አዳዲስና ጠቃሚ ሃሣቦችን የማፍለቅ፣ ለፓርቲው አመራር የማስተላለፍ፣ በፓርቲው እንቅስቃሴዎች ተግባሮች የመሳተፍ፣
14.1.5 ድርጅታዊ መዋቅርን ጠብቆ ሰለፓርቲው አሰራር ማብራሪያ መረጃ የመጠየቅና ሂስ የማቅረብ መብት አለው።
14.1.6 ማንኛውም አባል በራሱ ፍላጎት አባልነቱን መተው ይችላል።
14.1.7 ማንኛውም ዕጩ አባል በፓርቲው የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የመሳተፍ መብት አለው። ሆኖም የመምረጥ፣ የመመረጥና በውሳኔዎች ላይ ድምፅ የመስጠት መብት አይኖረውም።
14.1.8 የፓርቲው አባልነት በውርስ ሆነ በሌላ በማናቸውም መንገድ ለሌላ ተላልፎ የማይስጠ በአባሉ ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ነው።

14.2 የአባልነት ግዴታ፣

14.2.1 የፓርቲውን ዓላማ ፕሮግራምና ደንብ ተግባራዊ ማድረግ፣ ለሕዝብ ማስተዋወቅና ማስራጨት፣ የፓርቲውን እሴቶችና ልዩ መለያዎች ማክበር።
14.2.2 የፓርቲውን ፕሮግራም፣ ደንብና የሥነ ምግባር መመሪያዎች ማክበርና የፓርቲውን አመራር ውሳኔዎች ተግባራዊ ማድረግ፣
14.2.3 በተለያዩ ቋሚና ጊዚያዊ ኮሚቴዎችና ፓርቲው በሚጠራቸው የተለያዩ ስብሰባዎች የመሳተፍ፣
14.2.4 የአባልነት መዋጮን በወቅቱ መክፈልና በፓርቲው የገንዘብ መዋጮ ተግባራት በንቃት መሳተፍ። በፓርቲው ከተወሰነው ዝቅተኛ መነሻ አስበልጦ በመክፈል አርዓያ መሆን።
14.2.5 ሁሉም የፓርቲ አባላት በሚኖሩበት የምርጫ ክልል/ወረዳ በመራጭነት መመዝገብ ይኖርባቸዋል።
14.2.6 የፓርቲውን ዓላማ፣ የአሰራር መርሆዎች ከሚጎዱ ማናቸውም እንቅስቃሴዎች የሥነ ምግባር ጉድለቶች መቆጠብ፣
14.2.7 ለፓርቲው ታማኝ መሆን፣ የስብሰባ ሂደቶችና ሌሎች ዝግጅቶችን መግለፅ ከሚገባቸው በፊትና በሚመለከተው አካል ከመገለፁ በፊት ያለውን ከንውን በሚስጥርነት መጠበቅ፣

አንቀፅ 15. አባልነት የሚቋረጥበት ሁኔታዎች፣

15.1 የ .....ፓርቲን ለሚቃወሙ የፖለቲካ ድርጅቶች ተመራጮች ቅሰቀሳ ድጋፍ የሚያደርግ ወይም ከፓርቲ ውጭ በተመራጭነት የተመዘገቡ ግለሰቦች፤
15.2 ከ .....ፓርቲ ውጭ ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶችን የሚደግፍ አባል የሆነ፣ የ.....ፓርቲን ተመራጮች በተቀናቃኝነት ለምርጫ የተሰለፈ ወይም ይህን ለማድረግ በአደባባይ የገለጸ፤
15.3 የ ..... ፓርቲ አባል ሆነው የፓርቲውን ኦፊሴሊያው ተመራጭ ተጻረው በግላቸው ለመወርዳደር የተነሱና ይህን ከማድረግ እንዲቆጠቡ ከእጩ ተመራጮች የጥቆማ እለት በፊት የ2 ሳምንት ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው፤
15.4 በከፍተኛ ወንጀል ተከሰው የተፈረደባቸውና ለእስር በተዳረጉ አባላትና አባል ለመሆን በሚፈልጉ እጩዎች ላይ ብስኮ የሚከተሉትን መወሰን ይችላል።
15.5 በእስር በሚገኙበት ወቅት ከአባልነት ማገድ
15.6 ጉዳያቸውን ወደ ብሀተአኮ ለውሳኔ ማስተላለፍ፤
15.7 የፓርቲውን ደንብና የሰነስርአት ደንብ ተከትሎ ከአባልነት መሰረዝ ወይም በአባልነት እንዳይመዘገቡ የማድረግ ስልጣን አለው።
15.8 በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የአባልነት ግዴታቸውንና ሃላፊነታቸውን የማይወጡ አባላት ደንቡ በሚያዘው መሰረት ከአባልነት ሊታገዱ ወይም ሊሰረዙ ይችላሉ።
15.9 የ6 ወር የአባልነት መዋጮ እዳ ያለበት አባል ከአባልነት ይሰረዛል።

DRAFT

15.10በእዳ የተሰናበተ አባል ወደ አባልነት የሚመለሰው እዳው ከጀመረበት እለት አንስቶ ለመመለስ ጥያቄ እሰካቀረበበት እለት ያለበትን እዳ ከፍሎ ይሆናል።
15.11 የአባልነት ክፍያቸውን ያላሟሉ ከአንድ ወር በላይ እዳ ያለባቸው አባላት ለመመረጥም ሆነ ለምርጫ የሚወዳደሩ አባላትን ለመምረጥ አይችሉም።

አንቀፅ 16. ፋይናንስ እና ንብረት፣

16.1 የፓርቲው ዋንኛ የገቢ ምንጭ የአባላት መዋጮ እና ድጋፍ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ በሕግ በተፈቀደ መሰረት በፓርቲው ፋይናንስ የሚዘጋጅ ልዩ ልዩ ገቢ ማሰባሰቢያ እንዲሁም ከመንግስት የሚገኝ ድጋፍ ይኖረዋል።

16.2 ፓርቲው የሚሰበስበው ማንኛውም ገንዘብ በብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ጥቅም ላይ ይውላል። ለዚህ የሚሆኑ የፋይናንስ ሥርዓት ይዘረጋል።

16.3 የፋይናንስ ስርአቱ ፓርቲው በብሥአኮ እውቅና የተሰጣቸውና በሚገባ የተመዘገቡ የሚከተሉት አካዎንቲንግ አሃዶች ይኖሩታል።

16.3.1 ሁሉም የምርጫ ወረዳ የፓርቲ አባላት መዋቅሮች፤

16.3.2 ፓርቲው የፓርላማ አባላት፤

16.3.3 የፓርቲው ማእከላዊ ጽ/ቤት፤

16.3.4 የፓርቲው አለም አቀፍ ቻፕተር

16.3.5 እንዲሁም በብሥአኮ ፈቃድ የተሰጣቸው ሌሎች የፓርቲው አካላት፣

16.4 ከላይ የተዘረዘሩት አሃዶች በሚወጣ መመሪያ መሰረት ያልተማከለ የሂሣብ አስተዳደር ቢኖራቸውም፣ የሂሣብ እንቅስቃሴያቸውን ለብሥአኮ ወይም ለሚወክለው ሌላ አካል ሪፖርት ማድረግ ይኖርባቸዋል። ገዴታቸውን በማይወጡ አካላት ላይ አስተዳደራዊና ሕጋዊ እርምጃ ይወሳዳል።

16.5 የሪፖርት ማድረጊያ ጊዜ የአገሪቱን የበጀት መዝጊያ ወርና ቀን የተከተለ ይሆናል። (ከሐምሌ ፣- ሰኔ 30)

አንቀፅ 17. የፓርቲ ደንብ፣ ፕሮግራምና ፖሊሲዎች አጸዳደቅና አተገባበር፣

17.1 የፓርቲ ደንብ፣ ፕሮግራም፣ ሁሉም በፓርቲው የተለያዩ መዋቅሮች የተሰባሰቡ አባላት በየእርከናቸው በዝርዝር የመከሩበት ይሆናል።
የመጀመሪያው የፓርቲው ደንብ፣ ፕሮግራም በሁሉም የፓርቲው እርከኖች በውክልና ተመርጠው በመጡ የፓርቲው አባላት በጉባዔ ይጸድቃል።
17.2 የፓርቲ ፕሮግራም ፣ በየጊዜው በፖሊሲ ጥናቶች ላይ ተመስርቶ እየተሻሻለ የሚሄድ ይሆናል፤
17.3 የፕሮግራም ማሻሻል የጥናት ሃላፊነት ፓርቲው የሚያቋቁመው የፓርቲው ብሄራዊ የፖሊሲ ፎረም ይሆናል።
17.4 በፓርቲው ፕሮግራም የሚጨመር ወይም የሚቀነስ ማናቸውም ማሻሻያ አዲስ የፖሊሲ ሃሣቦች በፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ የተገኙት 2/3 ተወካዮች የድጋፍ ድምጻቸውን ከሰጡት ብቻ ተቀባይነት ያገኛል።
17.5 ፓርቲው ስልጣን ላይ ካልሆነ ከፓርቲው ፕሮግራም ወደ ምርጫ ማኒፌስቶ የሚካተቱትን የፓርቲውን ፕሮግራሞች የሚወስኑት የፓርቲው ብሄራዊ የስራ አሰፈጻሚ ኮሚቴ አባላት፣ የፓርቲው የጥላ ካቢኔ አባላት፣ የፓርላማ አባላቱ ኮሚቴ(የፓርቲው የፓርላማ አባላት በሌሉበት ወቅት የፓርቲው እጩ ተወዳዳሪዎች ኮሚቴና ሊቀመንበራቸው) የፓርላማ አባላት ሊቀመንበር፣ በብሄራዊ የፖሊሲ ፎረም ስር የተደራጁ የኮሚቴዎች ሊቃነመናብርትና ምክትሎቻቸው ይሆናሉ። ይህ ስብስብ በምርጫ ማኒፌስቶ ያልተካተቱ ነገር ግን በምርጫ ወቅት በሚነሱ ጉዳዮች የፓርቲውን አቋም የሚወስን ይሆናል።
17.6 ፓርቲው ስልጣን ላይ ከሆነ፣ ከፓርቲው ፕሮግራም ወደ ምርጫ ማኒፌስቶ የሚካተቱትን የፓርቲውን ፕሮግራሞች የሚወስኑት የፓርቲው ብሄራዊ የስራ አሰፈጻሚ ኮሚቴ አባላት፣ የፓርቲው የካቢኔ አባላት የፓርላማ አባላቱ ኮሚቴ፣ የፓርላማ አባላት ሊቀመንበር፣ በብሄራዊ የፖሊሲ ፎረም ስር የተደራጁ ኮሚቴዎች ሊቃነመናብርትና ምክትሎቻቸው ይሆናሉ። ከወረዳ አባላት ሃገር አቀፍ መዋቅር የክልል ቅርንጫፎችን የሚወክሉ አንዳንድ አባላት፣ አገር አቀፍ ማህበር ተወካዮች፣ ይህ ስብስብ ከምርጫ በፊት የሚዘጋጀውን የምርጫ ማኒፌስቶ የሚያዘጋጅ ይሆናል።

አንቀፅ 18፡ የጠቅላላ ጉባኤ የስነሰርአት ደንቦች

18.1 የጉባኤ ደንቦች - 1 የጉባዔ አጠራር፣

18.1.1 ብስኮ በአመት አንድ ጊዜ ጠቅላላ ጉባኤ ይጠራል። ጉባኤው የጠቅላላውን የፓርቲውን አምዶችና አባላቱን ሊያሳትፍ በሚችል፣ ለብዙሃኑ ተስማሚ በሚሆን ወርና ሳምንት ውስጥ እንዲሆን ይወሰናል። ይህ ውሳኔ በቋሚነት ይከበራል።

18.1.2 አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ በአስቸኳይ በሚጠራበት ወቅት በጉባኤው የመሳተፍ መብት ያላቸው የፓርቲው አካላት በሙሉ አስቸኳይ ምላሽ መስጠትና ተወካዮቻቸውን በመላክ መተባበር አለባቸው።

18.1.3 በአስቸኳይ የተጠራ ጠቅላላ ጉባኤ የሚያስተናግደው አጀንዳ ጉባኤውን ባሰቸኳይ እንዲጠራ ያደረገውን ጉዳይ የሚመለከት ብቻ ይሆናል።

18.1.4 ማንኛውም ጉባኤ እንዲሳተፍ የተወከለ አባል ከጉባኤው ጋር ተያያዥነት ያለውን ወጪዎቹን በሙሉ ይከፍላል። ይህን የሚከፍለው ለጉባኤ የወከለው የፓርቲው አካል ይሆናል። ክፍያው በብሥአኮ ተወስኖ ጉባኤው ከመደረጉ 2 ወራት በፊት የሚመለከታቸው አካላት እንዲያውቁት ይደረጋል። ክፍያ መፈጸም ያለባቸው አካላት ጉባኤው ከመደረጉ 1 ወር በፊት ክፍያውን ለብሥአኮ መላክ ይኖርባቸዋል። ለተወካዮች የስብሰባ ተሳታፊነት መታወቂያ ከመዘጋጀቱና ከመታደሉ በፊት ብሥአኮ የወሰነው የጉባኤ ተሳታፊነት ክፍያ መጠናቀቅ ይኖርበታል።

18.1.5 ወደ ጉባኤ በተወካይነት የሚመጡ አባላትን ስም ዝርዝርና አድራሻ ብሥአኮ በሚያወጣው የግዜ ሰሌዳ ውስጥ መላክ የወካዩ አካል ስራ ነው። የተወካይ ስምና አድራሻ ለመላክ ከተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ ውጭ ስማቸውና አድራሻቸው የተላኩትን ተወካዮች ጉዳይ መወሰን የብሥአኮ ስልጣን ይሆናል።

18.2 የጉባኤ ደንብ - 2፡ የሪፖርትና አጀንዳ አቀራረፅ፣

18.2.1 ብሥአኮ የፓርቲውን ያለፈውን አመት የስራ አፈጻጸም ጭማቂ ሪፖርታና የመጪውን አመት ስራዎች የሚያሳዩ ዘገባዎች ማቅረብ አለበት። ይህንና ሌሎችም በጉባኤው ላይ ውይይት የሚደረግባቸውን መሰረታዊ ሰንዶች አዘጋጅቶ በስብሰባ ተወካዮች እጅ ከጉባኤ ቀን በፊት ለሚመለከታቸው ተወካዮች ለሚልኩ የድርጅቱ አካላት እጅ እንዲደርስ ማድረግ የብሥአኮ ሃላፊነት ነው። ብሥአኮ ሰነዶችን የሚልክበትን ቀን የሚወስነው እራሱ ቢሆንም ቀኑ አባላት በሰነዶቹ ላይ መወያያት እንዲችሉ በቂ ጊዜ የሚሰጥ መሆን አለበት።

18.2.2 ብሥአኮ የብሄራዊ የፖሊሲ ፎረምን ሪፖርት ያቀርባል። ይህ ሪፖርት ያለፈውን አመት ፖሊሲ ነክ ስራዎችን ጭማቂና የሚቀጥለውን አመት የፖሊሲ ፎረሙን ስራዎች የሚመለከት ይሆናል። ይህ ሰነድ ከጉባኤ ቀን በፊት ለሚመለከታቸው ተወካዮች ለሚልኩ የድርጅቱ አካላት እጅ እንዲደርስ ማድረግ የብሥአኮ ሃላፊነት ነው። ብሥአኮ ሰነዶችን የሚልክበትን ቀን የሚወስነው እራሱ ቢሆንም ቀኑ አባላት በሰነዶቹ ላይ መወያያተ እንዲችሉ በቂ ጊዜ የሚሰጥ መሆን አለበት።

18.2.3 ማናቸውም የፓርቲው አካላት ለጉባኤ እንዲያዝላቸው የሚፈልጓቸውን አጀንዳዎች፣ የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያዎች የውሳኔ ሃሳቦች ለጉባኤው ማቅረብ ይችላሉ። እነዚህን አጀንዳዎችና የማሻሻያ የውሳኔ ሃሳቦች ከ250 ቃላት ባልበለጠ ጽሁፍ ከጉባኤው እለት በፊት ለፓርቲው ዋና ጸሃፊ መድረስ ይኖርባቸዋል። እነዚህ አጀንዳዎችና የወሳኔ ሃሳቦች ራሱ ብሥአኮ ለጉባኤ ከሚያቀርባቸው ጉዳዮች ስራ ያልተካተቱ መሆናቸውን አጣርቶ በጉባኤ ወይይት እንዲደረግባቸው የቀረቡ ጉዳዮችና የውሳኔ ሃሳብችን በቅደም ተከተል የማስቀመጡ ስራ የጠቅላላ ጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴው ይሆናል።

18.2.4 የተለያዩ የፓርቲው አካላት፣ በአመቱ ውስጥ ለብሥአኮና ለብሄራዊ የፖሊሲ ፎረም በድርጅት፣ በቅስቀሳና ሊሎችም ጉዳይች ላይ የሰጧቸውን ጥቆማዎች ምክረ ሃሳቦች በተመለከት የወሰዷቸውን እርምጃዎች ለጉባኤው ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለባቸው።

18.2.5 በጠቅላላ ጉባኤ መመረጥ ያለባቸውን የተለያዩ ኮሚቴዎች እጩ አባላትን በሙሉ ያዘጋጃል፣

18.2.6 ለጥቆማ የማቅረብ መብት የተሰጣቸው የፓርቲው አካላት በሙሉ የፓርቲው ዋና ጸሃፊ በሚያዘጋጀው ፎርማትና ብሥአኮ ባስቀመጠው የቀን ገደብ ውስጥ ጥቆማቸውን ለፓርቲው ዋና ጸሃፊ በጽሁፍ መላክ ይኖርባቸዋል። የጥቆማ መብት የተሰጣቸውን አካላት የሚዘረዝር ደንብ በጉባኤ አዘጋጆች ተረቆ በጉባኤ ይጸድቃል።

18.2.7 የፓርቲ መተዳደሪያ ደንቦች፣ ወቅታዊ የውሳኔ ሃሳቦችን፣ አስቸኳይ ወሳኔዎችንና ጥቆማዎችን ማቅረብ የሚችሉ የፓርቲው አካላት ፓርቲው የጣለባቸውን የገንዘብ መዋጮ በወቅቱ የፈጸሙ ብቻ ናቸው።

18.2.8 የፓርቲው አመታዊ ጉባኤ፣ በብሄራዊ ፖሊሲ ፎረም የሚቀርበውን ሪፖርትና የፖሊሲ ረቂቅ ሪፖርት ከማያቋርጥ የፕሮግራም ማሻሻያ ማእቀፍ ይመለከታል። የብስአኮ አመታዊ ሪፖርትና ፓርቲውን ለማበልጸግ ለማሳደግ የተቀረጹ ስትራተጂዎችን፣ በፓርቲው አካላት የቀረቡለትንና የተቀበላቸውን የህገደንብ ማሻሻያዎችን፣ የአስቸኳይ የውሳኔ ሃሳቦችን ያሰተናግዳል። ጠቅላላ ጉባኤ በብሥአኮ ወይም በጉባኤ አዘጋጆች ኮሚቴው ለውይይት እንዲቀርብ እውቅና ባልተሰጠው ማናቸውም ጉዳዮች ላይ አይወያይም።

18.2.9 ጠቅላላ ጉባኤ የፓርቲውን መታደራሪያ ደንቦችና ቋሚ መመሪያዎች የማሻሻል ውሳኔ ከወሰነ እነዚህ ወሳኔዎች ተግባራዊ መሆን የሚጀምሩበት የጊዜ ገደብ ይኖራል። ማናቸውም የማሻሻያ ውሳኔዎች ባስቸኳይ ስራ ላይ ቢውሉ ለፓርቲው ይጠቅማሉ ብሎ ብሥአኮ እስካልጠየቀ ድረስ ውሳኔዎቹ ቢያንስ ለአንድ አመት ተግባራዊ አይሆኑም።

18.3 **የጉባኤ ደንብ 3 - የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት፣**

በየትኛውም የፓርቲው መዋቅር የአመራሩ አመራረጥ በሚስጥር ድምፅ አሰጣጥ ይሆናል፤ በዚህ ደንብ ውስጥ ተለይቶ ከተደነገገው የድምፅ አሰጣጥ በስተቀር ማናቸውም ውሳኔዎች የሚወሰኑት በስምምነት ወይም በአብላጫ ድምፅ ይሆናል። ድምፅ እኩል ሲሆን በሰብሳቢው የሚደገፈው ወገን አሸናፊ ይሆናል።

በጠቅላላ ጉባኤ የተለያዩ ድምጽ አሰጣጦች ይኖራሉ። እነዚህም

1. እጅ በማውጣት የሚሰጥ ድምጽ፣
2. የአባልትን ድምጽ የሚያጸባርቅ የድምጽ አሰጣጣ በሚኖርበት ወቅት የአባላቱን ብዛት በሚያሳዩ ካርዶች አማካይነት፣
3. በሚስጥር መሰጠት የሚገባው ድምጽ በሚኖርበት ወቅት በድምጽ መስጫ ወረቀትና ድምጽ መስጫ ሳጥን አማካይነት የሚሰጡ ይሆናሉ።

በጉባኤ ላይ የትኞቹም ውሳኔዎች ከላይ በቁጥር ሶስት በተደነገገው የድምጽ መስጫ አግባብ እንደሚፈፀሙ ብሥአኮ ወስኖ ለጉባኤ አቅርቦ ያጸድቃል። በየትኛውም ወቅት የሚደረጉ አጠቃላይ ጉባኤዎች የሚከተሉት የድምጽ አሰጣጥ ከላይ የተዘረዘሩትን ይሆናል።

አንቀፅ 19. የፓርቲው ብሄራዊ የስራ አስፈፃሚ ሃላፊዎችና የብሄራዊ ኮሚቴዎች አባላት ምርጫ፣

19.1 ጠቅላላ መርህ፣

ማናቸውም የፓርቲው ሃላፊዎች፣ የፓርቲው ብሄራዊ ኮሚቴዎች አባላት፣ ምርጫዎች ፍትሃዊና ግልጽነት በተሞላበትና የድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብና ብሥአኮ ባሰቀመጣቸው አቅጣጫዎች የሚፈጸሙ ይሆናሉ።

19.2 የፓርቲ ሃላፊዎች አመራረጥ ሰነስርአት፣

19.2.1 አጠቃላይ
የሚቀጥሉት ስነስርአቶች፣ በብሥአኮ ስምምነት ማስተካከያ እስካልተደረገባቸው ድረስ ማንኛውንም የፓርቲ ሃላፊ የሚመረጥባቸው ደንቦች ይኖራሉ። ጥቆማን፣ የጊዜ ሰሌዳን፣ የተወዳዳሪዎችን የሰነምግባር ኮድና ሌሎችንም ተያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች በሚመለከት ብሥአኮ አቅጣጫ ያስቀምጣል። እጩዎች በፓርቲው የሃላፊነት ቦታዎች በተደራራቢነት እጩ ሆነው መቅረብ አይችሉም።
የፓርቲ መሪና የፓርቲ ምክትል መሪ ምርጫ

19.2.2 የፓርላማ አባላት መሪና ምክትል ይሆናል ያሏቸውን የጥንዶች እጩዎች በአንድ ላይ በእጩነት ጠቁመው ያቀርባሉ።

19.2.3 የመሪውና የምክትል መሪው ምርጫ አሰቀድሞ በሁሉም ድምጽ መስጠት መብት ባላቸው አካላትና አባላት ተካሂዶ ውጤቱም በጉባኤው ላይ ይነገራል። መሪውና ምክትሉ የሚመረጡት ግዴታቸውን በተወጡ አባላት አንድ አባል አንድ ድምጽ መርህ አማካይነት ይሆናል።

19.2.4 ሁሉም አባላት ብሥአኮ ባዘጋጀላቸው የድምጽ መስጫ ወረቀት አማካይነት ድምጽ ይሰጣሉ።

19.2.5 አባላት የሰጡት ድምጽ ለየብቻው ተቆጥሮ ይመዘገባል። ለጉባኤ አባላት ይፋ ይሆናል።

19.2.6 የድምጽ መስጠቱንና የደምጽ ቆጠራውን የማስተባበር ሃላፊነት በፓርቲው አደረጃጀት ስር የተደራጁ የምርጫ አስመራጭ አካላት ይሆናሉ። እነዚህ የምርጫ አካላት እንዴት እንደሚቋቋሙና ስራቸውን እንደሚያከናውኑ ብሥአኮ መመሪያ ይሰጣል።

19.3 ጥቆማ፣

19.3.1 የፓርቲው ሊቀመንበር/ምክትል ሆኖ ለማገልገል ፍላጎት ያለው ማንኛውም የዕጩነት መስፈርት የሚያሟላ አባል ዕጩ ሆኖ መቅረብ ይችላል።

19.3.2 በማንኛውም አካል የሚደረግ ጥቆማ የተጠቋሚውን ይሁንታ ማግኘት ይኖርበታል።

19.4 የፓርቲ የፖሊሲ ፎረም አባላትና የምርጫ ስርአት

19.4.1 የአባላት ብዛት በዘርፉ ስፋት የሚወሰን ሆኖ በባለሞያዎች የሚዋቀር ይሆናል።

19.4.2 የፖሊሲ ጥናትና ስትራቴጂ ፎረም ሰብሰቢና ምክትል ስብሳቢ በሊቀመንበሩ የሚመረጡ ሆነው፣ ሊቀመናብርት አባላትን መልምለው በየዘርፉ ያደራጃሉ። የዘርፉ ሰብሰቢዎች እና ምክትሎች በብሥአኮ ይፀድቃል።

19.5 ብሄራዊ ህገደንብ ተርጓሚና አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት የምርጫ ሥርአት፣

19.5.1 የእጩ አባላት ጥቆማና መስፈርት በብስኮ ተዘጋጅቶ በጠቅላላ ጉባኤ ይጸድቃል።

19.5.2 እያንዳንዱ ክልልና የፌደራል ከተማ በብህተወኮ ውስጥ በአንድ ተወካይ ይወከላል።

19.5.3 ለእያንዳንዱ ተወዳዳሪ በየምርጫ ወረዳው የተሰጠው ድምጽ ተመዝግቦ በጉባኤው ሰነድ ላይ ይሰፍራል። የምርጫው ውጤት በአመታዊ ጉባኤ በስነድ ተደግፎ ይፋ ይደረጋል።

19.5.4 ለብህተኮ የሚጠቆሙ አባላት ማናቸውም የአባልነት ግዴታቸውን የተወጡ መሆን ይኖርባቸዋል።

አንቀጽ 20: የጠቅላላ ጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴ አባላት የምርጫ ሥርአት፣

ጠቅላላ ጉባዔው በቀጣይ ለሚደረግ ምርጫ የጉባዔ አዘጋጅ ኮሚቴ በመሰየም ብሥአኮ መመሪያ አጽድቆ ይሰጣቸዋል።

አንቀፅ 21፡ ስለ ደንብ መሻሻል

ይህ ደንብ ሊሻሻል የሚችለው ማሻሻያው ለጠቅላላ ጉበዔ ቀርቦ በስብሰባ በተገኙ አባላት በ2/3 ድምፅ ተቀባይነት ሲያገኝ ነው።

አንቀፅ 22፡ ስለ ፓርቲው መፍረስ

ፓርቲው ከሚከተሉት ሁኔታዎች በአንዱ ከፖለቲካ ፓርቲነት ሊሰረዝ ይችላል።

1. በፓርቲው ህገ-ደንብ መሰረት ፓርቲው በራሱ ፈቃድ ከምዝገባ እንዲሰረዝ ሲጠይቅ እና በጉባዔ በ2/3 ድምጽ ድጋፍ ካገኘ፣
2. በህግ መሰረት/ በፍርድ ቤት ውሳኔ ሲሰጥ፣

አንቀፅ 23፡ የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

የዲስፕሊን ኮሚቴ በፓርቲው መዋቅር በየደረጃው ባልተቋቋመበት ሥፍራ በአባላት የሚፈፀሙ የዲስፕሊን ግድፈቶች በብሔራዊ ደረጃ በተቋቋመው በብህደተአኮ ታይቶ ውሳኔ ይሰጥበታል።

የፓርቲው የመጀመሪያ ጠቅላላ ጉባዔ የፓርቲው አደራጆች በሚያቋቁሙት የጉባዔ አዘጋጅ የሚወሰን ይሆናል። በተቻለ መጠን ይህን ደንብ በብቃት ለማስጀመር በሚያስችል መልኩ መመሪያ ይወጣል።

DRAFT

አንቀፅ 24፡ ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ
ይህ ደንብ በፓርቲው ጠቅላላ ጉባዔ ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል።

— 2011 ዓ.ም

DRAFT

DRAFT

DRAFT